# <u>የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ</u>

ጆከሮቹን ሰብስቦ
ዝሃር የእኔ ነው
አኪር እመታለሁ ብሎ
ቁማር ተጫውቶ
በራሱ ቁማር ተበልቶ
ዋጅጆ አየሁት
ባዶውን ቀርቶ

የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ
ሰለሞንን ጥበበኛውን
ፀሀይ በሰረቀ
እውነትን ለማስረሳት
የእውነት መርሻ ይዞ
ይታያል ፈዝዞ ተደናብሮ
ግመል ሰርቆ አጎምብሶ

የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ

ፈንጥዞ ነበር ተደስቶ
ጎል አስገባሁ ብሎ
የሁልጊዜ መጠቃትን መርሻ
በኳስ ጨዋታ ህግ
ኦፍሳይት መኖሩን ረስቶ
ዳኛ የማይቀበለው
የተመልካቹም መሳቂያ
ጎል አስገባሁ ሲል
ራሱ ተጫዋቹ ኦፍሳይት ነበር

የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ

ዘር ቆጥሮ
እንደ እንስሳ ወደ ክልል
ገብቶ ታግቶ
ላንግሊ ፓርክን
እንደ በተ ክርስቲያን መስጊድ ቆጥሮ
ዞር ብሎ ተሳልመው ሰግደው
የሰማዩን ገነት መርሻ
ምድራዊ ገነት ላንግሊ ፓርክ ነው ብሎ
ሞኝ አንዝህላል ከተገኘ
አታልሎ ሊያስኮንን
ተኮንኖ ሊያስኮንን
ከአቡኔ ጋር ሊፀልዩ
ከበየነ ጋር ካብዲ ካብዲ እያሉ
ላሌ ጉማይ ሲጨፍሩ
ጸሐይ ሳትወጣ ገብታባቸው

ሳትጠልቅ ጠልቃባቸው
አልታይ ብሏቸው ታውረው
በደም ላይ መጨፈሩን ቀጠሉ
በደም ላይ ጨፈሩ

የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ

ውሻ ቆብ ጭና እባብ መንኩሳ
ጅብ ሰማዕታት ሁኖ
ላንግሊ ፓርክ
እንደ ገነት ተቆጥራ
ይጋፋሉ ይጋፋሉ
ከጌታ ጎን ከጌታ ጎን
ጥሩ መቀመጫ ሊያገኙ
ዘንድሮስ ላንግሊ ፓርክ
ለሰማዩ መርሻ ሆነች
ላንግሊ ፓርክ
አንዲት ትንሽ ምስጢር
ልንገርሽ ላጫውትሽ
መጸሀፎቻችን የሚሉትን
እምነታችንና ትዕንቢታችን
ኢትዮጵያ እጆቿን የምትዘረጋው
ወደ ሳማይ እንጅ
ወደ ላንግሊ ፓርክ አለመሆኑን
ኢትዮጵያ ለዝንተ-ዓለም የኖረችው
ለዘለዓለምም የምትኖረው
በቆራጥ በጀግና ልጆቿና
በእምነት በአምላኳ ነው

የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ

ለትላንቱ አንጃ መርሻ አይሆንም
የአንጃን የካሃዲን ምንነት
ጠንቅቀን እናውቃለን
ደምተንበታል ሙተንበታል
ታስረንበታል ተሳደንበታል
የትላንቱም የዛሬውም አንጃ
አንድ ነው ዓላማ ዕምነቱ
ከርሱን ቀፈቱን ለመመላት
ቤተ መንግሥት ገብቶ
ፍርፋሪ ለመልቀም ለመቃረም
ንፁሃንን ለመግደል ለማስገደል
ማሳሰር ማሳደድ ነው
ሌላ ዕምነት የለውም
ዕምነቱም ተግባሩም
ወንጀለኝነት ነው

የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ

ደደብ ነው ከትላንቱ የማይማር
እንጅነር ዶክተር ነኝ አዋቂ ጥበበኛ
እያለ የሚወሸክት የሚቀላምድ
ለሆዱ ያደረ ክብሩን የሸጠ
የከሀዲ መንጋ
አዋቂ ከሆነ ጥበበኛ
እንዴት የረሳዋል
እንዴትስ ይረሳል
አንጃና ባንዳ
በገዛ ደሙ
እደሾቀ እንደሚሾቅ

የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ

አልገባውም እረስቶታል የትላንቱን
በገጠር በከተማ
ፋኖ  መሰማራት መቻሉን
እሳት ከነበረበት ረመጥ መኖሩን

የዘንድሮው አንጃ ደሳለኝ

በባንዳ በከሃዲ ምሁራን ላይ
ታሪክ እራሷን ስትደግም
አጉልቶ አሳየን !!

አንድ ኢትዮጵያ
አንድ ኢ. ሕ. አ. ፓ.

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!
ሞት ለባንዳ ለከሃዲ ምሁራን

ክፍል አንድ

ከአቸናፊ አራጋው

2000 ዓም